## ከተማ ፕላን የፕሮጀክት ቀረፃ የሥራ ሪፖርትን ይመለከታል፡፡

የሐረር ከተማ የተቀናጀ ልማት ፕላን ዝግጅትን አስመልክቶ የተከናወኑ ተግባራት፡

1. የመኖሪያ ቦታ ፕሮጀክት ቀረፃ ተከናውኗል፡፡
2. የገበያ ቦታ ፕሮጀክት ቀረፃ ተከናውኗል፡፡
3. የማዘጋጃ ቤት ገቢ ማሻሻያ ፕሮጀክቶች ማለትም
   - የንብረት ግብር ማሻሻያ ፕሮጀክትና
   - የመጨረሻ ቀረፃቸውን ይዘዋል፡፡
4. የማዘጋጃ ቤት የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ዝግጅት ለመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡
5. የከተማው የ10 ዓመት የመሬት አጠቃቀም ፕላን ተዘጋጅቷል፡፡
6. የከተማው የ10 ዓት የመንገድ ስርጭት ፕላን ተዘጋጅቷል፡፡
7. የተቀረጹ ፕሮጀክቶን ቦታዎች አመቺነታቸውን ማየት ነው፡፡
8. የከተማው የተፋስስ መስመር ፕላን /Drainage map/ ተከናውኗል፡፡
9. የከተማው አሰፋፈር የጥግግት ጥናት / Density/ተከናውኗል፡፡
10. በመስክ ሥራ ወቅት የተከናወኑት የፕሮጀክት ቀረፃዎች የማጠቃለያ ስራዎ በቢሮ ውስጥ ተከናውኗል፡፡
11. ከላይ በቀረቡት ስራዎች ላይ የቡድነን ውይይቶ ተካሄደው ከውይይቱ የተገኙት ጠቃሚ ሀሳቦች እንዲካተቱ ተደርገዋል፡፡
12. በተመሳሳይ ሁኔታ ከላይ የተገለጹት ስራዎች ለአጠቃላይ የመስሪያ ቤቱ ባለሙያዎች ለውይይት ቀርበው ጠቃሚ ሀሳቦች ተሰብስበዋል፡፡

## 3/ የሂሳብ አያያዝ እና የክፍያ አፈፃፀም ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮጀክት

ዓ ላ ማ፡-

በከተማዋ ዘመናዊና ቀልጣፋ የሆነ ተጠያቂነትን የሚያሰፍን ግልፅና ትክክለና የሂሳብ መግለጫ ማቅረብ የሚያስችል የሂሳብ አያያዝና የክፍያ አፈፃፀም ማሻሻያ ሥርዓት መዘርጋት፡

ግ ብ፡-

የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት የገቢና የወጪ መደብ /Chart of Accounts/ እንዲኖሩ ማድረግና እና የጥሬ ገንዘብ አስተዳድርና ክፍያ አፈፃፀም ማሻሻያ ሥርዓት መዘርጋት፡

ዋና ተግባር፡

የገቢና የወጪ መደብ /Chart of Accounts/ ማዘጋጀት እና የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር የክፍያ አፈፃፀም መመሪያና ማንዋል ማዘጋጃትና ማፅደቅ፡

## የሚጠበቅ ውጤት

በዚህ ፕሮጀክት በበጀት ዓመቱ የገቢና የወጪ መደብ ይዘጋጃሉ እንዲሁም የጥሬ ገንዘብ አስተዳደርና የክፍያ አፈፃፀም መመሪያና ማንዋል ተዘጋጅተው ይጠናቀቃሉ፡፡

4/ በከተሞች በኮምፒዩተር የተደገፈ የፋይናንስ አሠራር ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮጀክት.

## ዓ ሳ ማ፡-

የማዘጋጃ ቤቱ የፋ?አስተዳደር ሥርዓት በኮምፒዩተር የተደገፈ በማድረግ አሠራሩን ዘመናዊ እና የፋይናንስ መረጃ ፍሰትና ልውውጡን ቀልጣፋ እንዲሆን ማድረግ፡፡

## ግ ብ፡-

በኮምፒዩተር የተደገፈ የገቢ አሰባሰብ የበጀት ዝግጅት የሂሳብ አያያዝና የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ፡፡

## ዋና ተግባር

የ ICT Unit መመስረት የኮምፒዩተር እና ሌሎች ተጓዳኝ ዕቃዎች የፍላጎት ጥናት ማካሄድ እንዲሁም የIT ባለሞያዎች እንዲቀጠሩ ማድረግ፡፡

## የሚጠበቅ ውጤት

የ ICT Unit ይቋቋማል (አደረጃጀት) የቁሳቁስ ፍላጎት ጥናት ይካሄዳል ባለሞያዎም ይቀጥራሉ፡፡

5/ የገቢ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮጀክት

ዓ ሳ ማ:-

ተገቢውን የመሠረተ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት ለህብረተሰቡ ለማቅረብ እንዲያስችል ገቢን ለማጎልበት የሚረዱ ቀልጣፋነ ውጤታመ የሆነ የገቢ አስተዳደር አሰባሰብ አመዘጋገብና አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋት፡፡

ግ ብ:-

ከአገር አቀፍና ከክልል የታክስ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም በተጣጣመ መልኩ ገቢ ለማሳደግ የሚረዱ አሰባሰብና አጠቃቀም መመሪያና ማንዋል በማዘጋጀት በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ፡፡

ዋና ተግባር

በግልፅ መሰረት ላይ የተመሠረተ የማዘጋጃ ቤቱ ፍትሀዊ የግብር ምደባ የግብር ደግባኝ አቀራረብና አወሳሰን መመሪያ ማዘጋጀትና መተግበር፡

የሚጠበቅ ውጤት

በዚህ ፕሮጀክት የማዘጋጃ ቤቱ ገብር የሚሰበሰብባቸው የአፈፃፀም መመሪያና ማንዋል ተዘጋጅተው ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

6/ የከተሞች የበጀት ድጋፍና የብድር ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮጀክት

ዓ ሳ ማ:-

ካልተማከለ አስተዳደር አኳያ ግልፅ ፍትሃዊ እና አስተማማኝነት ያለው የፋይናንስ ሃብት ድልድል እና የብድር አቅርቦት ሥርዓት በመዘርጋት ከማዘጋጃ ቤቱን የፋይንንስ አቅም በጎልበት፡፡

ግ ብ:-

ፍትሃዊ ግልፅና አስተማማኝ የፋይናንስ /የበጀት/ ድጋፍ የሚገኝበትን እና በቂ የመሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፈንድ እንዲኖር ለማድረግ ከአገር ውስጥ ብድር የሚገኝበትን ሥርዓት መዘርጋት፡፡

ዋና ተግባር

በክልሉና በማዘጋጃ ቤቱ መካከል የገቢና የወጪ የፋይናንስ ኃላፊዎችን በአግባቡ በመለየት ክልሉ በማዘጋጃ ቤቱ እንደየሁኔታው የተለያዩ አይነቶች /ጥቅል በዐላማ ላይ የተገደበ/ የፋይናንስ ድጋፍ የሚገጥበትን ቀመር ማዘጋጀት፡፡

## የሚጠበቅ ውጤት

በክልሉና በማዘጋጃ ቤቱ መካከል የገቢና የወጪ የፋይናንስ ኃላፊዎች ይለያሉ ለማዘጋጃ ቤቱ ድጎማ የሚሰጥበት ቀመር ይዘጋጃል፡፡

7/ የኦዲት ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮጀክት

## ዓ ላ ማ፤-

ሀብትና ንብረት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ለመቆጣጠርና በየደረጃው ያለውን አካል ተጠያቂነት በማረጋገጥ የሚያስችል የተጠናከረ የውስጥ ኦዲት/ቁጥጥር ሥርዓት/ እንዲኖር ማድረግ እና የወጭ ኦዲት ውርዓትን በተጠናከረ መልኩ መዘርጋት፡፡

## ግ ብ፡-

የማ/ቤቱን የተጠናከረ የውስጥ ኦዲት ሥርዓት መዘርጋት፡፡

## ዋና ተግባር

ውስጥ ኦዲት አደረጃጀት ተጠናክሮ ይዘረጋል መመሪያና ማንዋል ተዘጋጅቶ ይተገበራል፡፡

## የሚጠበቅ ውጤት

ተጠናክሮ የተደራጀ የውስጥ ኦዲት ክፍል እንዲሁም በሥራ ላይ የዋሉ መመሪያና ማንዋል፡፡

# በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በ2000 በጀት አመት የመጀመሪያ ሪብ አመት የተቀናጀ የቤት ልማት ፕሮግራም፣የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ማስፋፊያ ፕሮግራም እንዲሁም የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፓኬጅ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት

## መግቢያ

በሐረር ከተማ ፈጣንና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ ወሳኝ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን ማጠናከር የተቀናጀ የቤት ልማት ፕሮግራም የማካሄድ ሥራዎች ተጠቃሽ ሲሆኑ የክልሉም መንግስት ለፕሮራሞቹ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ከ1998 ዓ.ም. ጀምተሮ ሰፊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

በሌላ በኩል በመመዝገብ ላይ ያለው ፈጣን ልማት ዘላቂነት ለማረጋገጥ በከተማው መልካም አስተዳደር ማስፈን ቁልፍ ጉዳይ በመሆኑ የሐረር ከተማ የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፓኬጅ ዝግጅት ተጠንቶ በተያዘው የ2000 በጀት አመት ወደ ትግበራ ይሸጋገራል፡፡

በአጠቃላይ የቤቶ ልማት የጥቃቅንና አነስተኛ ልማት እንዲሁም የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፕሮግራሞች የ2000 በጀት አመት የመጀመሪያ ሩብ አመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ክፍል 1. በክልሉ በመካሄድ ላይ የሚገኘው የተቀናጀ የቤት ልማት ፕሮግራም የ2000 በጀት አመት የመጀመሪ ሪብ አመት ዕቅድ አፈፃፀም :

ክፍል 2 የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ከማስፋፋት አኳያ በክልሉ በ2000 በጀት አመት የመጀመሪያ ሪብ አመት ዕቅድ አፈፃፀም፡

ክፍል 3 የሐረር ከተማ የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፓኬጅ በ2000 በጀት አመት የመጀመሪው ሩብ አመት የስራ ክንውን፡

የሐረር ከተማ የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፓኬጅ በፌደራል ሥ/ከ/ል/ሚኒስቴር ከተዘጋጀው ሰነድ መነሻ በማድረግ ጠከተማውን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የተዘጋጀ ሲሆን በፓኬጁ የታቀፋትን ንዑስ ፕሮግራሞ የሚያዘጋጁ ኮሚቴዎች ፕሮግራሞቹ በቀጥታ በሚመለከታቸው ቢሮዎ የተቋቋሙ ሲሆን ፓኬጅ የሚያስተባብር እስትሪንግ ኮሚቴም ተቋቁሞ የፓኬጁ ዝግጅቱን ስራ ሲከታተል ቆይቷል፡፡

በፓኬጅ ዝግጅቱ ወቅት ከፕሮግራሙ ጋር ተያያዥነት ካላቸው እንደ ሶቪል ሰርቪስ ሪፎርም እና የፍትህ ስርአት ማሻሻያ ፕሮግራም ሥራዎች ጋር በማስተሳሰር ለመፈፀም በሚያመች መልኩ የተቀረፀ ሲሆን የፓኬጅ ዝግጅቱ ከተጠናቀቀ በኋላም የክልሉ ካቢኔ በፕሮግራሙ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ የተሰጡትን የማሻሻያ ነጥቦች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል ለፌደራል ሥ/ከ/ል/ሚኒስቴር በተዘጋጀው የከተማው የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፓኬጅ ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተልኳል፡፡

በአጠቃላይ በአሁኑ ወቅት የየንዑስ ፕሮግራሞ የ2000 በጀት አመት ዕቅድና ዝርዝር የፋይናንስ ፍላጎት ተዘጋጅቶ የተጠናቀቀ ሲሆን በበጀት አመቱ የመጀመሪያ ሩብ አመት የየንዑስ ፕሮራሞቹ የሥራ ክንውን በተመለከተ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

11. አደረጃጀትና የሰው ኃይል ሥርዓት ማሻሻያ ን/ፕሮግራም የመልካም አደረጃጀቶች እንዳይኖር ከተማው የሚያስፈልገውን ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል በመዘርጋት በየጊዜው በራሱ አቅም የሚሠራበት ሁኔታ ለመፍጠር በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን 4 አባላት ያሉበት የንዑስ ፕሮግራሙ አስፈፃሚ አካል የተቋቋመ ሲሆን በን/ፕሮግራሙ የተከናወኑ ተግባራት የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

- በሥ/ከ/ል/ሚ/ር የተዘጋጀውን ረቂቅ መነሻ በማድረግ ካለን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተጣጥሞ ተዘጋጅቷል፡፡
- የን/ፕሮግራሙ የ2000 እቅድ ተዘጋጅቷል፡፡
- የን/ፕሮግራሙ የ 2000 በጀት አመት የድርጊት መርሀ ግብር ከበጀት ፍላጎት ጋር ተዘጋጅቷል፡፡

I. <u>የህዝብ ተሳትፎ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም</u>

በሐረር ከተማ አስተዳደር የቀጥያ የሕዝብ ተሳትፎ ዲሞክራሲያን በማስፈን ነዋሪዎችን የሥልጣን ባለቤትና የልማት ተጠቃሚ ለማድረግ ከ2000-2002 ባሉት 3 ተከታታይ አመታት ተግባራዊ የሚሆን የሕዝብ ተሳትፎ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም የተዘጋጀ ሲሆን በውስጡም የሚከተሉትን 2 ፕሮጅክቶች ያቀፈ ነው።

1. የቀበሌ ምክር ቤቶች አቅም ግንባታ ፕሮጀክት ክልላችን ከሌሎ ክልሎች በተለየ መልኩ አንድ ከተማ ያላት በመሆኑ የክልሉ ም/ቤት የከተማው ም/ቤት ጭምር በመሆን እያገለገለ ይገኛል። ስለዚህ ከፌደራል ሥ/ከ/ል/ሚ/ር ከተዘጋጀው የከተሞች ም/ቤት አቅም ግንባታ ፕሮጀክት የተቀረፀ ሲሆን በአሁኑ ወቅት አጠቃላይ ዝግጅቱ ተጠናቆ በተያዘው የ2000 በጀት አመት ወደ ትግበራ ይሸጋገራል።
2. የሕዝብ ተሳትፎ አቅም ግንባታ ፕሮጀክት ይህ ፕሮጀክት እንደ ቀበሌ ም/ቤቶች አቅም ግንባታ ፕሮጀከት ሁሉ ዝግጅቱ ተጠናቆ በተያዘው በጀት አመት ወደ ትግበራ የሚሸጋገር ሲሆን በስሩ ከተካተቱት ተግባራት በፌደራል ሥ/ከ/ል/ሚ/ር በተዘጋጀው ሰነድ ላይ ከተዘረዘሩት ተግባራት በተጨማሪ ከተማዋ በአለም አቀፍ ደረጃ ከተመዘገቡ ታሪካዊ ቦታዎች አንዷ እንደመሆኗ መጠን ህዝቡን ታሪካዊ ቅርሶቹን እንዲጠብቅ ቀጥተኛ ተሳትፎ ለማድረግ የሚያስችለው ተግባት እንዲካተቱ ተደርጓል።

በአጠቃላይ ንዑስ ፕሮግራሙን በተመለከተ ለክልሉ ካቢኔ ለውይይት ቀርቦ ገንቢ አስተያየቶች የተሰጡ ሲሆን እነዚህን አስተያየቶች በማካተት የ2000 በጀት አመት ዕቅድ እንዲሁም ፍላጎት የተጠናቀቀ ሲሆን ንዑስ ፕሮግራሙ ወደ ትግባራ ከመሸጋገሩ በፊት ለተያዩ የህብረተሰብ አካላት ማለትም ለ130 ዕድርና አፎቻ አመራር አካላት፣ለ158 የሙያ ማህበር አመራር አካላት፣ ለ80 ሌሎ ማህበር አካላት፣ ለ76 ቀበሌ አመራር፣ለ105 ወጣት ማህበር አመራር አካላት፣ ለ203 የሲቪክ ማህበራት አመራር አካላት እንዲሁም ለ2463 የልማት ቡድን አመራሮች በአምስት ዙር የሚካሄድ ኝዑስ ፕሮግራሙን ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ተዘጋጅቷል።

## III. <u>የከተማ ፕላን ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም</u>

የከተማ ፕላን ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም በሐረር ከተማ የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፓኬጅ ስር ከታቀፉት ንዑስ ፕሮግራሞ አንዱ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የንዑስ ፕሮግራሙ ዝግጅት ተጠናቆ ወደ ትግበራ በመሸጋገር ላይ ይገኛል። በመሆኑም ፕሮግራሙን በተመለከተ በ2000 በጀት አመት የመጀመሪያ ሩብ አመት ለተከናወኑ ስራዎች እንደሚከተለው ቀርቧል።

ክልላችን ከሌሎች ክልሎች በተለየ መልኩ አንድ ከተማ ያላት በመሆኑ በፌደራል ደረጃ በንዑስ ፕሮግራሙ ሥር ከተቀረፁት 3 ፕሮጀክቶች ውስጥ የአነስተኛ ከተሞች ልማት ፕሮጀክትን በማውጣት የከተማ ፕላን አቅም ግንባታ እና የከተማ ነክ መረጃ ስርዐት ዝርጋታ የሚባሉ ሁለት ፕሮጀክቶች የያዘ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የንዑስ ፕሮግራሙ የ2000 በጀት አመት ዕቅድና የፋይናንስ ፍላጎት ዝግጅት የተተናቀቀ ሲሆን ወደ ትግበራ በመሸጋገር ላይ የሚገኝ ስለሆነ የ 2000 በጀት አመት የሚከናወኑ ተግባራትን የዘት ላይ ያተኮረ ነው።

1. <u>የከተማ ፕላን አቅም ግንባታ ፕሮጀክቶች በ2000 በጀት አመት የታቀዱ ዋና ዋና ተግባራት ይዘት</u>

- የከተማ ፕላን ተቋም ማቋቋም በተመለከተ በክልሉ አንድ ከተማ ያለ በመሆኑ እና ለሌሎች ከተሞ የሚሰጡ እገዛዎች ባለመኖራቸው ተቋሙን ከማቋቋም ይልቅ

በን/ኢ./ከ./ል/ቢሮ የሚገኘው የከተማ ልማት ድጋፍ ሰጪ መምሪያን በሚገባ ማጠናከሩ አላስፈላጊ የሰው ኃይል እና ሐብት እንዳይባክን ያደርጋል፡፡

-

**<u>በሰኔ ወር 1999 ዓ.ም. የሐረር ከተማ የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ፓኬጅ ስር የታቀፉትን ንዑስ ፕሮግራሞችን በተመለከተ በክልሉ ካቢኔ ባደረገው ስብሰባ ሳይ የተሰጡ ዋና ዋና የማሻሻያ ነጥቦች</u>**

1. የሕግ ማዕቀፍና የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም በተመለከተ- የከተማ ነክ ጉዳዮችን የሚያይ ፍርድ ቤት ማቋቋም የሚለውን የከተማ ነክ ጉዳዮችን የሚያይ ችሎት በመደበኛ ፍርድ ቤት ማቋቋም በሚል ማሻሻያ ሐሳብ እንዲተካ፣
2. ፋይናንስና የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም በተመለከተ- ንዑስ ፕሮግራሙ የከተማው ማዘጋጃ ቤትን ፋይናንስ ነክ ጉዳዮችን ባካተተ መልኩ እንዲዘጋጅ፣
3. የአደረጃጀት እና የሰው ኃይል ሥራ አመራር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም በተመለከተ - ከPSCAP ሥር ከተያዙ ዕቅዶች ጋር በተቀናጀ መልኩ እንዲዘጋጅ፣
4. የህዝብ ተሳትፎ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም በተመለከተ - የከተማ ም/ቤት ምርጫ ማካሄድ የሚለው የክልሉ ም/ቤት የከተማው ም/ቤት በመሆኑ በዚህ ረገድ ማስተካከያ እንዲደረግ፣
5. የከተማ ፕላን ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም በተመለከተ- በውስጡ የተካተቱት ተግባራት ከሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር ፕሮግራሞች ጋር በተመጣጣመ መልኩ እንዲዘጋጁ፣
6. የመሬት ልማትና አስተዳደር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም በተመለከተ- በንዑስ ፕሮግራሙ የታቀፉት 4 ፕሮጀክቶች ለአተገባበር በሚያመች መልኩ የአፈፃፀም መርሐ-ግብራቸው እንዲስተካከሉ፡፡ የሚሉት ዋናዋና የማሻሻያ ነጥቦች ሲሆኑ፡-

* የመሠረተ ልማት አገልግሎትና አቅርቦት ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም በተመለከተ በስሩ የተዘረዘሩ ተግባራት ከሞላ ጎደል በፌደራል ደረጃ በሚገኙ የተለያዩ መ/ቤቶች የሚተገበሩ መሆናቸውን በውይይቱ ሳይ ተብራርቷል፡፡